መግቢያ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የመጀመሪያ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተማሪዎች የሚሰጡ የላብራቶሪ ትምህርት ውጤታማ ለማድረግ ለረጅም ጊዜ ከመምህርነት ሙያ ውጭ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩትን የላብራቶሪ ባለሙያዎች ከድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ከሚተዳደሩበት ስርዓት ሽግግር ሳይደረግ መቆየቱ ለሁለተኛ ደረጃ እና ለከፍተኛ ትምህርት የሚዘጋጁ ተማሪዎችን ውጤታማ የሆነ የላብራቶሪ አገልግሎት እንዳያገኙ ሲያደርጋቸው ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጉዳዩን በዝርዝር በማጥናትና የሳይንስ ላብራቶሪ በባለቤትነት ስሚት እንዲመራ በመምህርነት ሙያ ውስጥ መሆን እንዳለበት መጋቢት 7 ቀን 2012 በቁጥር አ2.2./6651/ከ28-40135 ያቀረበውን ጥያቄ በዝርዝር በማየት የፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ የሚከተለውን መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

የተፈፃሚነት ወሰን

- ይህ መመሪያ የሚመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከ5-8ኛ ክፍል እና ከ9-12ኛ ክፍል ለሚገኙ የላብራቶሪ ባለሙያዎች ብቻ ይሆናል፡፡

1. የላብራቶሪ ባለሙያዎች ወደ መምህርነት ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ፣

1.1 የትምህርት ዝግጅት በተመለከተ ፡-

- የላብራቶሪ ባለሙያዎች በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከ 5ኛ-8ኛ ክፍል ለመመደብ የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ9ኛ-12ኛ ክፍል በመምህርነት ለመመደብ በሁለተኛ ዲግሪ በሙያው ሊኖራቸው ይገባል፡፡
- በባዮሎጂ፣ በፊዚክስና፣ በኬሚስትሪ የትምህርት ዓይነት በማስተማር ሙያ ወይም የማስተማር ሙያ ስልጠና /PGDT/ የወሰዱ ወይም ጀምረው በሂደት ላይ የሚገኙ ሆነው ቢያንስ አንድ ሰሚስተር የተማሩ መሆን ይኖርበታል፡፡